# እኔ የድሃ ልጅ ነኝ

# ልጄ ግን የሓብታም ልጅ ነው

በኣንድ ሓብታም ሰውየ ድርጅት የሚሰሩ ሰዎች ነበሩ። ሰራቶኞቹ የሆነ ነገር ለመግዛት የሓብታሙ ልጅ ሲልካቸው ዕቃውን ኣምጥቶ ይዘውት የመጡትን መልስ ለሻይ ለቡና ይሁናቹህ እያለ ኣይቀበላቸውም። ኣንድ ኣንዴም ከኪሱ እንደዛ እያለ ገንዘብ ይሰጣቸዋል። ሓብታሙ ሰውየ ሲልኳቸው ግን ይዘውት የሚመጡትን መልስ .05 ሳንቲምም ብትሆን ይቀበልዋቸዋል ይቆጣጠርዋቸዋል። ሰራቶኞቹ በኣባትና ልጅ ያለውን የተለያዩ ባህሪ ግራ ስያጋባቸው ሰራቶኞቹ እንዲህ ብሎ ሓብታሙን ሰውየ ጠየቁ። ልጅህ የዋሕ ነው ችርጋችን ኣይቶ ይረዳናል የሆነ ነገር ለመግዛት ሲልከን የምናመጣው መልስ ለሻይ ለቡና እያለ ኣይቀበለንም። ኣንተ ግን የልጅህን ያህል ኣይደለህም። ለምንድ ነው? ብሎ ሲጠይቋቸው። እውነታቹህ ነው እኔ የድሃ ልጅ ነኝ ልጄ ግን የሓብታም ልጅ ነው። ብሎ መለሰላቸው ይባላል። ሓብታሙ እኔ ድሃ የድሃ ልጅ በመሆኔ ይህንን ገንዘብ እንዴት ኣድርጌ ለፍቸ እንዳመጣሁት ኣውቀዋለውሁ። ልጄ ግን ይህ ገንዘብ እንዴት እንደመጣ ስለማያውቅ ነው ችላ ብሎ የሚበትነው ለማለት ነበር እኔ የድሃ ልጅ ነኝ ልጄ ግን የሓብታም ልጅ ነው ብሎ የመለሱላቸው።

ከላይ እንደ መግብያ የወሰድኩት ለሚቀጥለው 4ተኛው በኢትዮጵያ ለሚካሔደው ምርጫ ኣስመልክቶ የኢህኣዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ነገር የወደብ የዓንቀፅ 39ና ኢህኣዴግ በሚያካሒደውን የዓቅም ግንባታ ኣስመልክቶ ያላቸውን ኣቋም ስከታተል በሁሉም የተቃዋሚ ድርጅቶች የተገነዘብኩት ዋናው ችግር ከምን የመነጨ ይሆናል ብየ ሳሰላስልና ሳስብ የመጣልኝ መልስ ለመስጠት ከመፈለግ ነው ሓብታሙ የድሃ ልጅ ያሉትን ያስታወስኩት።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢህኣዴግ ለሰራውና ለፈጠረው ኣዳዲስ ዕድገቶች ምንም እንዳልተሰራ ስያወሩ ሰምተናል። በኢትዮጵያ መብት እንደ ማይከበር ሰዎች ሓሳባቸው በነፃ መግለፅ እንደማይችሉ በጤና በትምህርት ምንም ነገር እንዳልተሰራ በተለይ በኣንድ ኣንድ ጉዳዮች የንጉስ ሃይለስላሴና የደርግ መንግስትታት ከኣሁኑ መንግስት እንደሚሻሉ ሳያፍሩ የተናገሩ ድርጅቶችም ኣሉ። የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታን ማየት ያቃታቸው ለምንድነው? በኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ለውጦቹ መኖራቸው እንኳን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የውጭ ዓለሙ ሕብረተሰብም ሳያቅማሙ የመሰከሩት ሓቅ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ይንን ሓቅ ማየት ካልቻሉ መንግስትነት ብያገኙም ትክክለኛው የኢትዮጵያና የዓለም ሁኔታዎች

ለማየት ኣቅም ስለ የሌላቸው እንዴት ይሆን ኢትዮጵያን ለመምራት የሚወዳደሩት?

ኣንድ ሓይል የጠላቱን ኣወንታና ኣሉታ እውነተኛ እውቀት እንኳን ባይኖረው ውጤቱን በራሱ ላይ የውድቀት ስልትና እስትራተጂ ማውጣት ያህል ነው የሚሆነው። በሌላ ኣነጋገር ኣንድ ስራ ለመስራት ብቃት ስለ እማይኖረው ወዳቂ ነው። ይህንን ከታሪክ ውደኋላ ተመልሰን ሩቅ ሳንሔድ በኢትዮጵያ የነበረውን ነገር መመልከት ይቻላል።

ከ35 ዓመታት በፊትና እስከ የደርግ መንግስት ውድቀት ግዜ በሃገራችን በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች ነበሩ። ከህወሓት/ኢህኣዴግ ጋራ በነበራቸው የዓላማ ልዩነት ህወሓትን እናሸንፈዋለን ምንም ኣያመጣም የትም ኣይደርስም በማለት በህወሓት ላይ ጦርነት ከፍተው በከፈቱት ጦርነት የተሸነፉ እነማን እንደ ነበሩና ለምን እንደተሸነፉ ታሪክ የመለሰው ጥያቄ ነው። ያ ስሕተት ታሪክ መዝግቦት ኣልፈዋልና። የዛን ግዜ መንግስት ደርግም ጭምር ሓይሉን በመተማመን በህወሓት/ኢህኣዴግ የተዛባ ኣመለካከት በመያዝ ጥቂት ወንበዴ በማለት ጦርነት ውስጥ ገብቶ ተሸንፈዋል። ሁሉም ሓይሎች ለውድቀት የዳረጋቸው በህወሓት/ኢህኣዴግ ትክክለኛውን እውቀት ማየት ባለመቻላቸው ነው። ለምን ነበር የህወሓት/ኢህኣዴግ እውነተኛ ማንነት ለማየት የተሳናቸው? ብሎ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል። መልሱ ደግሞ የተወሳሰበ እንቆቁልሽ ኣይደለም። እነዛ ሓይሎች የህወሓት/ኢህኣዴግ ሓቀኛው ማንነት ማየት የሚቹልበት ተፈጥሮና ባህሪ ስላልነበራቸው ብቻ ነበር ብቸኛው ችግራቸው። የኣሁን ግዜ እኛ እንበልጣለን ባዮች ተቃዋሚ ድርጅቶችም ያንን ዓይነት ችግር ውስጥ ነው ያሉት። በነገራችን ላይ በርካታ ሰዎች በኢህኣፓ በመኢሰን ደርግና ሌሎች ውስጥ የነበሩና በህወሓት/ኢህኣዴግ የተሸነፉ በኣሁን ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥም ይገኛሉ።

እነዚህ ሰዎች ኣንዱን ሲሰሩ ሲከሽፍባቸው። ሌላው ብያደራጁ ቢጠፋባቸው ሌላው ጋር ቢገቡ ሲበላሸባቸው በተደጋጋሚ የታዩ ሰዎች ጥቂቶች ኣይደሉም። ከዛ ወደዛ የሚያዳርሳቸው ምኑ ነው? የጀመሩት ሁሉም ነገር ለምን ኣልተሳካላቸውም? እነሱ የሚሰጡትን መልስ ምን እንደሚሆን እንጃ። ትክክለኛው መልስ ግን እውነተኞች ታጋዮች ስላልሆኑ ነው። እውነት የሚባል ነገር እንኳን ሊከተሉት በኣጠገቡም ሰለኣላለፉ ነው ትክክለኛው መፍትሔ በየገቡበት ማምጣት ያቃታቸው። ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ ኣያጣፍጥም የሚለውን ኣባባል በትክክል ምን ማለት መሆኑን ካለማወቃቸው ነው ካለ ዕረፍት ሁሉም ያዳረሱት። ከዚህ ምርጫ በኋላም በሌላ ስም ተደራጅቶ ብቅ እንደሚሉም ለመተንበይ ኣያዳግትም። ስራ ያጡ መነኩሴ ቆባቸው ቀድዶ ይሰፋሉ እንደተባለው የእኛ ፖለቲከኞች ደግሞ ኣንዱን ነገር ስያደራጁ ስያፈርሱ በሌላ ሲተኩት ነው ግዜ ማሳለፍ የሚያውቁት እንጂ በጀመሩት ስራ ለማሳካት እጅጉን መድከም ኣይችሉም። ችግሮች ስያጋጥማቸው መሸሽ እንጂ ያንን ችግር እንዲወጡት የሚያስችል ሞራልና ልቦና ፍፁም የላቸውም። እንዲህ የሚሆኑት ለምን ይሆን? ብሎ

መጠየቅና መመለሱን ተገቢ ይመስለኛል። የእነሱ ኣጀንዳ ለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ መፍትሔ ማምጣት ሳይሆን ብቸኛው ኣጀንዳቸው ስልጣን ብቻ ስለሆነ ነው ኣንዱ ጋ ሳይሳካላቸው ሲቀር ሌላው ጋ በሌላ ሙኮራ እንደ ኣዲሶች ሁሌ ብቅ የሚሉት። እዛም ጋ ሳይሆንላቸው ሲቀር ሌላው ጋ መጠጋት ወይም ማደራጀት ይፈልጋሉ። ለዚህ ቀላሉ ማስረጃ ኣለኝ። በመድረክ ውስጥ መድረክን በሊቀመንበርነት የሚመራ በየ 4 ወር ይቀየራል ይተካል። ለምን በየ4 ወር መተካካት ኣስፈለገ? ብሎም መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። መልሱ ሁሉም ሰዎች የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ የፈጠሩት ዘዴ እንጂ ስኬታማ የስራ ውጤት ኣለው/ያመጣል ተብሎ የተፈጠረ ነገር ኣይደለም። በየዓመታት ብያደርጉት ሁሉም ጋ ማዳረስ ይቸግራል። ስለዚህ በየ 4 ወራት ሲሆን ለሁሉም በተፋጠነ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ልክ እንደ ጠበል ስልጣንም ሁሉም ጋ መድረስ ስላለበት።

ዓሰብን እናመጣለን የሚለውን ኣሰልቺ ቀልዳቸው በጣም ስያማሙቁት ሰንብተዋል በክርክሩ ግዝያት። እኔ የገረመኝ ቢኖር ስለ መልካም ኣስተዳደርና ዴሞክራሲ ሲወራ ዓሰብን መኀብኘት። ስለ መድበለ ፓርቲ ሲወራ ዓሰብን ማንሳት ስለ ያልተማከለ ፌደራሊዝም ሲነሳ ዓሰብ ማምጣት ስለ ዲፕሎማሲ ሲነገር ዓሰብን መጥራት። ኢህኣዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ኣጀንዳ የላቸውም ማለቱ እውነቱን ነው። ትምህርትና ጤና ኣስመልክቶ የነበረውን ክርክር ኣልተከታተልኩትም እዛም ስለ ዓሰብ ሳይነሳ ያለፈ ኣይመስለኝም ሳስበው። የትምህርትና የሕክምና ዘመናዊ መሳርያዎች በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ የዓሰብ ወደብ ባለቤት ባለመሆናችን ምክንያት ሆነዋል በማለት ዓሰብን ያነሱ ይመስለኛ። ምክንያቱ ዓሰብ በሓሳብ ካላላመጡ የሚያቀርቡት ንግግር ለእነሱ ጣዕም የለውማ።

እንዴት ዓሰብን ማምጣት እንደሚቻል ግን የሰጡት ኣሳማኝ ሓስብ የለም። መንግስትነት ከያዝን የሚሉት ልክስክስ መልስ ግን ኣላቸው። ኣሳማኝ መልስ ማምጣት ኣይችሉም። ይህንን እነሱም ኣሳማኝ ነገር ማቅረብ እንደማይችሉ በሚገባ በትክክል ያውቃሉና። ታድያ ለምንድነው የዚህን ቀልድ ኣዝማሪዎች የሆኑት? ሌላ ቁምነገር የላቸውም ኣጀንዳቸው ከዓሰብና ዓንቀፅ 39 ኣልፎ ጥሩ ሓሳብ ልያወሩ ፍፁም ኣይችሉም። ቁምነገር የሚባል ነገር የላቸውም። ስለዚህ የግድ ኣንድ ነገር ይዘው መቅረብ ኣለባቸው በህዝብ ፊት። ትክክልም ባይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ወሰን የለህ የወደብ ፍላጎት ስለኣለው ወደብ በሚለው ቃል ምክንያት ሰብከን ብቻ ነው በጎናችን ማሰለፍ የምንችለው የሚለውን የተዛባ ኣመለካከት ስለ ኣደረባቸው ነው ዘመናዊያን የወደብ ሰባኪዎቻችን ዓሰብ ሳያነሱ መናገር ፍፁም የማይችሉት። መንግስትነት ብይዙ ግን መጣም ዕርግጠኛ ነኝ ስለ ወደቡ ሁለት ኣማራጭ ብቻ ነው የሚኖራቸው። ምናልባት ጦርነት ማወጅ ወይም ዓሰብ ማስመለስ ኣይቻልም ምክንያቱ ኢህኣዴግ ያበላሸው ጉዳይ ስለሆነ ብሎ ነገሩ ማድበስበስና ኢህኣዴግ ማወንጀል ብቻ ይሆናል የሚያረጉት።

ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ኢትዮጵያን ለመምራት በምንም ዓይነት መስፈርት ከኢህአዴግ የሚበልጡበት ምንም ነገር መገንዘብ የሚያስችል ስራ ይቅርና ሓሳብም የላቸውም። እስከ አሁን የተገነዘብኩት ያላቸው ዓቅም ያልሆነውን ማውራት ካልሆነ በስተቀር። ለተቃዋሚ ድርጅቶች ወደብ ማምጣት ከማንኛው ነገር ቀላል አደርገው የማቅረብ ቆንጆ ቀልድና በቂ ዕውቀት እንዳላቸው ሳልመሰክርላቸው አላልፍም።

ኢትዮጵያን መምራት ለተቃዋሚ ድርጅቶች በጣም ቀላል ነው። እንደ ሚያስቡት። ያ ስራ ግን ምን ያህል ጥረት እንደሚያስፈልግ በሚገባ የተገነዘቡት አይመስሉም። ለዛም ነው ኢህአዴግ ለሚሰራቸው በሙሉ የሚቃወሙት። ለምን ድህነት አልጠፋም ዓይነቱ አመለካከት ያላቸውም ይመስላሉ። ለምን ብይባል የሓብታም ልጆች ስለሆኑ። በየ የውጭ ሃገራት ኤምባሲ እየሔዱ ኢህአዴግ ያወነጅላሉ። ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልገባቺው አሁን ግን በተቃዋሚ ድርጅቶች እንድትሆን አጥብቆ ዕርዳታን ይሻሉ ከውጭ ሓይሎች። ዘመናዊ የቅኝ ግዛት ዘዴ ማለቴ ነው። እስከ አሁን ተከብራ የቆየቺው ኢትዮጵያ አሳልፎ ለመስጠት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ይሞክራሉ። ለምን? ኢትዮጵያ እስከ አሁን ተከብራ እንድትቆይ ያደረጋትን ምን ያህል እንደ ተሰዋላት ስለማያውቁ እንደ የሓብታሙ ልጅ ስለሆኑ።

ተቃዋሚ ድርጅቶቹ የሚፈልጉት ስልጣን ላይ መውጣት ብቻ ነው። እንዴት? ጉዳያቸው አይደለም። በውጭ ሓይሎች የሚመጣውን የኢትዮጵያ ዕድል እነሱ ስልጣን እስካገኙ ሌላው የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ጉዳያቸው አይደለም። እነሱ ያልደከሙለት ያልሞትለት ነገር ስለሆነ አይገባቸውምና። ስለዚ እንደ የሓብታሙ ልጅ እነሱም ኢትዮጵያ ገበያ ላይ አውጥቶ መሸጥ ለእነሱ ምንም አይደለምና።

እንዴትስ ስለኢትዮጵያ ያስባሉ? መንግስት በሚያደርገው ነገር በሙሉ ከመቃወም በስተቀር ሌላ ስያደርጉ መቸ ተገኙና። መንግስት ለሚሰራው መደገፍ የሚባል ነገር በእነሱ ዘንድ ነውር ነው በምንም መልኩ አያውቁትም። መቃወም ብቻ ነው ሞያቸውና። ቁምነገር ለመስራት መታደል ያስፈልጋል። የአስተሳሰብ መታደል። ይህንን ደግሞ ከባህሪ ነው የሚመነጨው።

ልጁ በአባቱ ሓብት ያንን ያህል ጥንቁቅ ባይሆንም ከመስራት ግን አልቦዘነም። አባቱ ያን ሓብት እንዴት እንዳመጣው ባያውቅም በአባቱ ሓብት አይቀልድም ይሰራል። ስለዚህ የአባቱን ሓብት ለማሳደግ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ እንዳለ ወይም እንደነበረ መናገር ይቻላል።

የኢህአዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሰላማዊ መንገድ መታገል እንዲችሉ ያደረገ ከሰማይ በወረደ በረከት ሳይሆን በኢህአዴግ የትጥቅ ትግልና በተከፈለው መስዋእት ነው አሁን የፈለጉትን ሓሳብ ካለ ገደብ

መናገር የቻሉት። እንደፈለጉት መደራጀት የቻሉት። ኢትዮጵያ አሁን የደረሰቺው ዕድገት እንድትደርስ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንደ ድርጅትም እንደ ግለ ሰውም የዛን ዕድገት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያደረገው የኢህአዴግ መንግስት ብቻ ነው። ይህንን ማየት ወይም መቀበል ግን አልቻሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች። እንድያውም በተቃራኒ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ሉኣላውነት ምንም ሓላፊነት እንደማይሰማው ኢትዮጵያ ካለ ወደብ እንድትኖር እንደ አደረጋት። ኢትዮጵያ የሚበታትን የኢትዮጵያን ኣንድነት የሚያናጋ እንደ ኣንዲት ኣገር እንድትኖር የማይፈቅድ ፖሊሲ እንዳለው አድርገው ነው ኢህኣዴግን የሚፈርጁት። በኢትዮጵያ የተገኘው በኢኮኖሚ በፖለቲካ በማሕበራዊ በወታሃደራዊና ዲፐሎማሲያዊ የተቻለውን ያህል አጥጋቢ ውጤቶችና ለውጦች እንደ ተመዘገበ በሚገባ ያውቃሉ። ተጠቃሚዎች ናቸውና። ኢህኣዴግ ለውጥ ኣምጥተዋል ግን አይሉም የእናታቸው ጡት ነካሾች ናቸውና።

ይህንን እያወቁ ታድያ እንዴት ምንም እንዳላዩ ምንም እንዳልተሰራ ደረታቸው ነፍቶ ያወራሉ? ይህንን ከሁለት ነገር መተንተን ይቻላል። ኣንደኛው ትምክህት የወለደው በትግራይ ሰው እንዴት እንመራለን ከሚለው ቆሻሻ ኣመለካከት የሚመጣ ሲሆን። ሁለተኛው ደግሞ ባዕዳውያን ለማስደሰት ተብሎ የሚደረግ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው። ሁለቱም ምክንያቶች ከኣንድ ዋነኛ ምክንያት ይመነጫሉ። በፈለገው መንገድና ምክንያት ስልጣን ላይ መውጣት ነው በእስትራተጂ ደረጃ ለዛ ኣሉባልታ የሚነሳሱት። የሓብታሙ ልጅ በኣባቱ ላይ መጥፎ ኣያስብም። ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ግን ለኢህኣዴግ ምስጋና እንኳን ኣይሰጡትም። ለውጥ ተገኝተዋል ለውጥ መጥተዋል ብሎ በእነሱ ኣንደበት መናገር ግን ለእነሱ ሓይለኛ ውርደት ይሆንባቸዋል። የሚፈልጉትን ስልጣንም የሕልም እንጀራ መስሎ ይታያቸዋል የኢህኣዴግ መልካም ስራ ብያወሩ። ከጀርባ ያሉት ኣይዛቹህ ባዮችም ይከዱዋቸዋል። በራሳቸው ኣይተማመኑም በህዝባቸው ኣይተማመኑም። በኢትዮጵያ ለውጥ ወሳኝ ሚና ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን ገና ኣልገባቸውም። እነሱ የሚያኑት ባዕዳውያን ብቻ ነው ለስልጣን የሚያበቁን ብሎ ነው የሚኖሩት።

ሌላው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ኣቶ ገብሩ ኣስራት ኣቶ ስየ ኣብርሃ ወ/ሮ ኣረጋሽ ኣዳነ በኢህኣዴግ የኣማራር ኣባላት በነበሩበት ወቅት ስለ ወደብና ስለ የብሔር ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን ከልብ ተቀብለውና ኣምነው የሰሩበት ኣሁን ደግሞ ተሳስተን ነበረ በማለት ኣሁንም መንግስት ለመሆን እንቅስቃሴ ላይ ናቸው። ለመሆኑ እነሱ እንደሚሉት በበለፀጉ ኣገሮች የሚመሩ የመንግስት ባለስልጣኖች እንኳን በሃገር ላይ ስህተት በትዳራቸው ላይ ስህተት ሲፈፅሙ ከመንግስት ስልጣን መባረር እንደሚገባቸውና እንደተባረሩ ብዙ ኣብነቶች ማስቀመጥ ይቻላል። ይህንን በትራዳቸው ላይ ክህደት ሲፈፅሙ ነው። በኣገር ላይ ክህደት የፈፀመ ደግሞ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ለመገመት ኣያስቸግርም።

የእኛ ፖለቲከኞች ግን በእነሱ ኣመለካከት ኣገርን የሚያክል የጎዳ ስራ ሰርተው ይቅርታ ጠይቆ ኣሁንም ለመንግስትነት እየተዘጋጁ ይገኛሉ። መንግስት እነሱ እንደሚሉት በኣገር ላይ ስተት ፈፅመውና መንግስትም የበኩሉ ያመነበት በኢህኣዴግና በመንግስት ላይ ስህተት የፈፀሙ እነዚህ ሰዎች በፖለቲካ ተደራጅተን የኢህኣዴግ ተቃዋሚ ፓርቲ እንሆናለን ብሎ ሲጠይቁ ኢህኣዴግ ፈቅዶላቸው እየተንቀሳቀሱ ነው። ኢህኣዴግ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ኣይደለም በማለትም ግን እያወገዙትም ነው። ዴሞክራሲያዊ መንግስት ካልሆነ ኢህኣዴግ ታድያ እንዴት ነው ሓሳባቸው እንደፈለጉት ለመግለፅ ለመደራጀት የቻሉት?

ተቃዋሚ ድርጅቶች በኢህኣዴግ የተገኘውን ለውጥ መነሻ ኣድርገው እንደ የሓብታሙ ልጅ ሳይሆኑ መሆን የሚገባቸው በኢትዮጵያ ተሓድሶ ሓልፊነት ወስደው የጎደለውን ፈልጎ ኣግኝቶ የበኩላቸውን ኣስተዋፅኦ ማድረግ ነው የሚገባቸው። ያንን የሚያገኙትን ቀዳዳ በድርጅታቸው ዓቅም መሙላት እንኳን ባይችሉ ዓቅሙ ላለው መንግስት ቀዳዳውን በማሳየት መፍትሔ እንዲ ደረግላቸው ነው ማድረግ የሚገባቸው። ምናልባት መልካም ኣመለካከት ይዘው ተፈላጊ ዓቅምና ብቃት ፈጥረው መንግስት የሚሆኑበት ግዜ ኣሁን እንኳን ባይሆን ኣንድ ቀን ሊመጣ ይችላል። ያ በሚሆንበት ግዜ ከዜሮ ኣይሆንም መነሳት ያላቸው። ይህንን የማድረግ የማንኛው የተቃዋሚ ሓላፊነት ነው መሆን የሚገባው።

በኢትዮጵያ የተመዘገበው ለውጥና ዕድገት ኣሁን ካለበትም መብለጥ ይችል ነበር ብየ እገምታለሁ። ሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ከመንግስት ጋራ ተባብሮ መስራት በቻሉ ኖሮ። ኣሁን በትክክል እየታየ ያለውን ግን ማደናቀፍ እንደ ትልቅና ዋነኛ ሞያ በተያዘበት ሁኔታ ነው ያለው ትክክለኛው የተቃዋሚ ድርጅቶች ስራ።

ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዳሉበት እስከ ቀጠሉ ድረስ በኢትዮጵያ መንግስት ለመሆን የሚበቁበት ግዜና ኣጋጣሚ ፍፁም ኣይኖርም። የውድቀትና የድህነት ኣጋሮች ናቸውና። ውስጣቸው በሚገባ መፈተሽ ቀዳሚው ዋነኛ ስራቸው ኣድርገው ማየት ይገባቸዋል። በተለይ በተለይ ለኢትዮጵያ እድገት ትክክለኛው መፍትሔ የሚመጣው ከኢትዮጵያ ውስጥ እንጂ ከውጭ ኣለመሆኑም በሚገባ ማወቅና ማመን ያስፈልጋቸዋል። ችግር ካለ ችግሩ መፍታት የሚቻለው ከውስጥ በዜጎች እንጂ ከውጭ በውጭ ዜጎች ኣለመሆኑም ከልብ ማወቅ ያስፈልጋል። የውጭ ሓይሎች የመጀመርያው መመለስ የሚፈልጉት ነገር በሚሰሩት እነሱ በምን መልኩ በዋናነት ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ነው። በይበልጥ ከሌላው ይልቅ እነሱ እንዴት ይጠቀማሉ ነው። እንሱ የማይጠቀሙበት በምንም ተኣምር ኣይገቡበትም። እንደዛ መሆናቸው ስህተት ኣይደለም። ጥቅም በሌለበት ለምንስ ይገባሉና? በኢትዮጵያ ውስጥ ለለውጥ መፍትሔዎች ማምጣት የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነው የመፍትሔው ባለቤት። ሓቁን እንዲህ እያለ ግን ባዕዳውያን ጋ ሔዶ መስገድ ኣያስፈልግም። “እናትዋን ትታ ኣሰሪዎችዋን ትናፍቃለች” ዓይነት

የመሆን ስራ ተቃዋሚዎች ብያቆሙት ጤነኛ መንገድ መያዝ ያስችላቸዋል።

ከኢህኣዴግ ታሪክ ብዙ ነገር መማር ይቻላል። በኢህኣዴግ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች በትጥቅ ትግል ዘመናቸው ስለ ኣንድ ነገር ማንሳት ይቻላል። ህወሓት ከኢህኣፓ ጋራ ሳይጋጩ ደርግን ከስልጣን ለማውረድ በየድርጅታቸው በጋራ የሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ ሓሳብ ስያቀርብ ኢህኣፓ እኔ ነኝ ታላቁ ድርጅት በመንገዳችን በፕሮግራማችን ነው ህወሓት መመራት ያለበት ብሎ ኣሻፈረኝ ብሎ ከዛም ኣልፎ ህወሓትን ለማጥፋት ተንቀሳቀሰ። ህወሓት ግን ኣቅሜን ኣነስተኛ ነው ለኢህኣፓ ኣሜን ብየ መገዛት ኣለብኝ ያለበት ግዜ ኣልነበረም። ሻዕብያ ጀብሃና ሌሎቹም ህወሓት ለማንበርከክ ያላደረጉት ሙኮራ ኣልነበረም። ኢህዴን ከኢህኣፓ ጋ ታግሎ የኢህኣፓ የጥፋት መንገድ ለማስተካከል የቻለውን ያህል መስዋእትም ከፍሎ ሳይሳካለት ሲቀር ትክክለኛውና ብቸኛው መፍትሔ በመውሰድ ለብቻው መታገልን ጀመረ። ኦህዴድ ከኦነግ ጋራ በየድርጅታቸው ሆነው ግን ደግሞ በጋራ ፖለቲካዊ ትግል ለማካሔድ ፈተነ ኣድርጎ ኦነግ ብቸኛው የኦሮም ህዝብ ድርጅት ኦነግ ስለሆነ ኦህዴድ የራሱን ፕሮግራም ትቶ በኦነግ ስር ታቅፎ ትግሉን እንዲቀጥል ያቀረቡለትን መፍትሔ በመቃወም ታገለ።

የኢህኣዴግ መስራች ድርጅቶች በዓላማቸው ጠንካራ እምነት በመገንባትና ትክክለኛው የትግል ኣቅጣጫ በመንደፍ ለማንኛውም ሓይል ተገዢና ተንበርካኪ ሳይሆኑ ለድል በቅተዋል። ለምን በራስ መተማመን ትክክለኛው መንገድ ስለወሰዱ ይህንን ትግል የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ነው ህዝቡን በጎናችን ኣሰልፈን ለድል እንበቃለን በሚለው ብቸኛውና በትክክለኛው መንገድ መጓዝ ስለቻሉ ነው ለድል የበቁት። ኣሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ካለቺው ድሃ ኢኮኖሚ ለኣንዴና ለመጨረሻ መውጣት የሚቻላው ባልተሰላቸ ውጣ ውረድና ትግል ህዝቡን ኣሰልፎ ብቻ እንጂ ለባዕዳውያን በመስገድና በመንበርከክ ኣለመሆኑ ኢህኣዴግ ያመነው ገና በረሃ በትጥቅ ትግል ዘመኑ ነው።

ኣንድ ኣንድ የኢህኣዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ኢህኣዴግ ልክ እነ ሻዕብያ እንደ ሚያራምዱት ኢህኣዴግ የዛን ኣገር መልእክተኛ ነው። የተላከውን ከመፈፀም ኣልፎ የግሉ የሚያደርገው ነገር የለውም። በሶማል የኢትዮጵያ የመከላከልያ ሓይል የተላከው የኣመሪካን ስራ ለማስፈፀም ነው ወዘተ እያሉ ኢህኣዴግን ስያወንጅሉት ሰምተናል። በተለይ በኢህኣዴግ መንግስት በከፍተኛ ስልጣን የነበሩ ሰዎች ይህንን ወሬ ስያራግቡ በተደጋጋሚ ይሰማሉ። ኢህኣዴግ ግን እንዳዛ ለውጭ ሓይሎች ምን ግዜም ተገዢ ሆኖ የታየበት ኣንድም ቀን ትሁን የለችም። ታሪክ መስክሮት ያለፈ ነገር ነው። ለዚህም ነው የውጭ ሓይሎች የተለያዩ ምክንያቶች እየፈጠሩ እያበጠሩ ኢህኣዴግን ለማወንጀል ቀንና ማታ ነገሮችን እየፈጠሩ ያሉት። በኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኣይከበርም። ኢትዮጵያ የምትሰራቸውን የሓይድሮ ኤለክትሪክ ግድቦች ጉዳት ያመጣሉ። የኢትዮጵያ መንግስት

በስልጣን 18 ዓመታት ስለቆየ ኣምባገነን መንግስት ነው። ወዘተ እያሉ ኢህኣዴግን እያወገዙ እንጂ እያሞጎሱ ኣይደለም ያሉት። ለምንድነው እነዛን የውጭ ሓይሎች በኢህኣዴግ ላይ የሚዘምቱት? ለሃገራችን ካላቸው መልካም ኣመለካከት ነው የሚል መልስ እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ። ለኢትዮጵያ ህዝብ ካላቸው መልካም ምኞት ነው ብለው የሚመልሱ ሰዎች ካሉ በጣም ደካሞች መሆናቸውን ነው የሚገልፀው።

መልሱ የውጭ ሓይሎች ወይም መንግስታት ኢህኣዴግን ከገመቱት በላይ ከቁጥጥራቸው ውጭ ስለሆነባቸው ነው። ለምሳሌ ያህል በቻይናና ኢትዮጵያ ያለውን ግንኙነት ኣመሪካውያን ወደው የተቀበሉት ነገር ኣይደለም። ግን ኣማራጭ የላቸውም ሳይወዱ መቀበል ይኖራቸዋል። ኢትዮጵያን ማጣት ኣይፈልጉምና። ከቻይና መቀራረብ ኣይገባቹህም ብሎ በይፋ መናገር ኣይችሉም ግን በሌላ መንገድ ወይም ዘዴ ያንን ነገር እንዲነግሩህ ይፈልጋሉ። ኣንዱ ከሚያደርጉት ነገር በሰብኣዊ መብት ረገጣ ብሎ ነገር ፍለጋ ይገባሉ። ኢህኣዴግ ኢትዮጵያን የሚመራው ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይጠቅማል ከሚለው መሰረታዊ ጥያቄ በመነሳት እንጂ ለውጭ ሓይሎች ወይም መንግስታት ምን ይጠቅማል ከሚለው መርህ ነገሮች ለመስራትና ለማከናወን ሌትና ቀን ብሎ የሰራበት ግዜ ከቶ የለም። ኢህኣዴግ እነሱን በማይፈልጉት ተጉዞ ኢትዮጵያን ከገባችበት የኢኮኖሚ ደህነት ለማውጣት የሚያስችለውን ስራዎችን እየሰራ የሚያጋጥሙትን ችግሮቹን ተቋቁሞ እየተጓዘ ነው። ኢህኣዴግ ምን ግዜም በኢትዮጵያ ተደራድሮ ለባዕዳውያን ኣሳልፎ የሰጠበት ወቅት የለም። ለወደፊቱም ኣይኖርም። እንደ ሓብታሙ የድሃ ልጅ ኢትዮጵያ ለዚህ ደረጃ እንዴት እንደደረሰች በሚገባ ያውቃልና። ለምን ኢህኣዴግ የድሃ ልጅ እንጂ የሓብታሙ ልጅ ስላልሆነ።

የኣሁኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ወይም የኢህኣዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከኢህኣዴግ ከብዙ ኣንዱ መማር ያላቸው ነገር ቢኖር በህዝባቸው መተማመን ዋነኛውና ብቸኛው ለህዝብና ኣገራቸው መቆማቸው መመዘኛ ነጥብ ነው።

የኣባቱን ሓብት እንደሚያባክን የሓብታሙ ልጅ መሆን ትተው ግን ከየሓብታሙ ልጅ ደግሞ ኣባቱን የማገዙን ኣወንታ ስራ ተምረው ኢትዮጵያ ለማሳደግ ኢህኣዴግ ብያግዙ ደህነትን በማጥፋት የተፋጠነ ውጤት እንደሚያመጡ ኣምነው የበኩላቸውን ኣስተዋፅኦ ብያደርጉ መልካም ነው። የጥፋቱን መንገድ ለይቶ መውሰድ ኣያውቅም ለሁሉም ነው ጥፋት የሚያደርሰው። በህዝብ ላይ ጥፋት መፈፀም በራስህ ላይ ጥፋትን ማፋጠን ነውና ታምሞ ከመማቀቅ ኣስቀድሞ መጠንቀቅ እጅጉን ያስፈልጋል።

ከሃይለ/ተጋዳላይ
ኣውስትራልያ gedliweyn@yahoo.com